# ነብያቶቻችንን እንወቅ

እንዴት ናችሁ! አንድ ቀን ሁላችሁም ታድጋላችሁ፡፡ መጀመሪያ ወጣት ትሆናላችሁ በመቀጠል ልክ እንደ አክስቶቻችሁና አጎቶቻችሁ ትሆናላችሁ፡፡

አሁን በእድሜ ገፋ ያሉ ሰዎችን  እማማ ወይም አባባ ብላችሁ ትጠሯችኋላችሁ፡፡ አንድ ቀን ሰዎች እናንተንም ልክ እንደዚህ ይጠሯችኋል፡፡

አንድ ቀን ልክ እንደ አያቶቻችሁ ታረጃላችሁ፡፡ በመጨረሻም ይህንን አለም ለቃችሁ ወደሚቀጥለው አለም ለመኖር ትሄዳላችሁ፡፡

ወደፊት ስራ ለመያዝ ት/ቤት ትሄዳላችሁ፡፡ ለወደፊት ኑሮአችሁ አሁን ዝግጅት ታደርጋላችሁ፡፡ ጥሩ! ለቀጣዩ አለም ኑሮስ ምን ማዘጋጀት እንዳለባችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ?

በርግጥ በሚቀጥለው አለም ደስተኛ ህይወት ለመኖር አሁን ማከናወን ያለባችሁ ተግባራት አሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እነዚህ ስራዎች ምን እንደሆኑ በቁርዓን አማካኝነት ነግሮናል፡፡

ለዚህም ብፁዕ ስነ-ምግባር ያላቸውን ነብያቶች በመምረጥ አላህ ከሰዎች ምን እንደሚፈልግ ሰዎችን እንዲያስተምሩ ልኳቸዋል፡፡

ነብያቶች የተላኩባቸው ህዝቦች አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ ተጣርተዋል፡፡ ሰዎች አላህን ካላመለኩ እንደሚቀጡም አስጠንቅቀዋቸዋል፡፡

በላቀ ባህሪያቸው እና ስነምግባራቸው ነብያቶች ለሰው ልጆች ተምሳሌት ናቸው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ለፈጣሪ ባላቸው ቅርበትና በጥንቁቅ ባህሪያቸው አማካኝነት ነው፡፡

ከነብያት የህይወት ታሪክ ትምህርት እንድንወስድ አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ ነግሮናል፡፡

"ታሪካቸው በእርግጥ ለአስተዋዮች ተግሳፅ እና ትምህርት ሰጭ ነው። ቁርአን የተቀጠፈ ወሬ አይደለም። ግና ከርሱ በፊት የነበሩ መለኮታዊ መልዕክቶችን አፅዳቂ እና ሁሉንም ነገር ገላጭ ለአማኞችም መመሪያና አዝነት ነው።"(ሱራ ዩሱፍ: 111)

አሁን የተወሰኑ ነብያትን እንመልከት።ለህዝቦቻቸው ምን እንዳስተማሩ እንይ።ካከናወኗቸው ተግበራትም እንደ ምሳሌ ልንወስዳቸው የሚገቡ ነገሮችን እንወቅ።

## ነብዩ ኑህ

ነብዩ ኑህ የተላኩባቸው ህዝቦች በአላህ (ሱ.ወ) ከወረዱት እውነታዎች ያፈነገጡ ነበሩ። በአላህ ከማመን ይልቅ የተለያዩ ነገሮችን ያመልኩ ነበር።

ኑህ (አ.ሰ) የሁሉም ነገር ፈጣሪ አላህ መሆኑን እና ከሱ ውጪ ማንንም እንዳያመልኩ ነገሯቸው። ይህ ካልሆነ አላህ ሊቀጣቸው እንደሚችል አስጠነቀቋቸው። ይህም በአንድ የቁርአን አንቀጽ ተጠቅሷል።

> "ኑህን ወደ ህዝቦቹ ላክን። "እኔ ለናንተ ግልፅ አስጠንቃቂያችሁ ነኝ" የሚል የጥሪ ድምፁንም አሰማ። "አላህን እንጂ አታምልኩ። እኔ የአሰቃቂውን ቀን ቅጣት እፈራላችኋል።" አላቸው" (ሱረቱል ሁድ፡25-26)

ነገር ግን በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው የነብዩላህ ኑህን ጥሪ የተቀበሉት። ከዚህ በኋላ አላህ ነብዩ ኑህን ትልቅ መርከብ እንዲሰሩ አዘዛቸው።

> " "በኛ ጥበቃ ስር ሆነህና የምንሰጥህን መመሪያ ተከትለህ ጀልባዋን ስራ"። ...የሚል መልዕክት አወረድንለት።" (ሱረቱ አልሙዕሚኑን ፡27)

በአላህ ያላመኑት ሰዎች ምንም ባህር ሳይኖር ኑህ መርከብ በሚሰሩበት ጊዜ በጣም ተደንቀው አሾፉባቸው።ሆኖም እነዚህ ከሀዲዎች ቅጣት ሊደርስባቸው እንደሆነ አላወቁም ነበር።

መርከቡ ተሰርቶ ሲጨረስ ለብዙ ቀናት ከባድ ዝናብ ዘነበ። መሬትም ውሀ ማፍለቅ ጀመረች ይህ ከከባዱ ዝናብ ጋር በመደባለቅ ግዙፍ ጎርፍን ፈጠረ። ውሀው ሁሉንም ነገር በመሸፈኑ ምክንያት መሬት ወደ ባህርነት ተቀየረች።

አላህ (ሱ.ወ) ኑህን አማኞችንና የተወሰኑ እንስሳትን ወደ መርከቧ እንዲጭኑ አዘዛቸው።

ወደ ኑህ መርከብ ላይ ከወጡት ሰዎች በስተቀር ሁሉም ሰዎች ሰመጡ፡፡ በቁርአን ላይ እንደተጠቀሰው ጎርፉ ካቆመ በኋላ መርከቧ ከፍ ባለ ቦታ ላይ አረፈች፡፡

በቴሌቭዥን የተለያዩ ሀገሮች የተከሰቱ ጎርፎችን አይታችሁ ይሆናል፡፡ እነዚህ አደጋዎች ሲከሰቱ ሰዎች እርዳታ ለማግኘት ጣራዎቻቸው ላይ ይወጣሉ፡፡ የሞተር ጀልባዎችና ሂሊኮፕተሮች ብቻ ናቸው ሊረዷቸው የሚችሉት፡፡

በነብዩላህ ኑህ ዘመን ከኑህ መርከብ ውጭ ሰውን ሊያድን የሚችል ነገር አልነበረም፡፡

ይህ አደጋ የኑህ ጎርፍ ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ ኑህን የካዱ ህዝቦችን ለማጥፋት በአላህ (ሱ.ወ) የተላከ መቅስፍት ነበር፡፡

በኑህ ላይ ካመፁት ከነዚህ ዕብሪተኛ ህዝቦች ውስጥ አንዳቸውም ወደ መርከቧ አልገቡም፡፡ ከአላህ ሌላ ባሉ ነገሮች በመመካት እነሱ የሚያድኗቸው መሰላቸው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ካልፈለገ የትኛውም ነገር ሊያድነን አይችልም፡፡

ህዝቦቹ ይህንን ባለማወቃቸው ከፍ ወዳሉ ቦታዎች እና ተራራዎች ወጡ፡፡ ነገር ግን ግዙፍ በሆነ ማዕበል ሰመጡ፡፡

## ነብዩላህ ሙሳ

ከአለማችን የጥንት ስልጣኔዎች መካከል የጥንታዊ ግብፅ አንዱ ነው፡፡ በሶስት ሺህ ምዕተ አመት አካባቢ ግብፃውያን መፃፍን ተማሩ፡፡ ለስልጣኔያቸውም የናይል ወንዝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበረከተ፡፡

ናይል የአፍሪካን አህጉር በማቋረጥ ብዙ ገፀ በረከቶችን በመያዝ ወደ ግብጽ ይፈሳል፡፡ስለዚህ ግብፆች በዝናብ ጊዜያት ላይ ብቻ ሳይመሰረቱ አዝርዕትን ማሳደግ ይችላሉ፡፡

በዚህም ምክንያት የጥንታዊ ግብፅ መሪ ፈርኦኖች የተደራጀ ግዛትን መሰረቱ፡፡

ከፈርኦኖች አብዛኛዎቹ በአላህ የማያምኑና እራሳቸውን እንደቅዱስ የሚቆጥሩ እብሪተኛ ግለሰቦች ነበሩ፡፡

ፈርኦኖች ጨካኝ በመሆናቸው ሰዎችን ባሪያ በማድረግ በመጥፎ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲሰሩ ያስገድዷቸው ነበር። እንዲሁም አላህን ከማምለክ ይልቅ ለተለያዩ ጣኦታት ይሰግዱ ነበር።

አላህ (ሱ.ወ) ነብዩ ሙሳን ወደዚህ ቦታ ላካቸው። ነብዩ ሙሳ የተላኩት ግብፅ ትክክለኛ እምነት ትቀበል ዘንድ ለመጥራትና የእስራኤል ህዝቦችን ከባርነት በማውጣት ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ለመምራት ነበር።

ሙሳ እና ወንድማቸው ሀሩን ከሀዲና አምባገነን የሆነውን ፈርአውንን በመጋጠም አላህን እንዲያመሰግንና እንዲገዛ ጋበዙት። ይህ የሙሳ ግብዣ በአንድ የቁርአን አንቀጽ ተጠቅሷል።

> **"ሙሳ፡- "ፈርአውን ሆይ! እኔ የአለማት ጌታ መልዕክተኛ ነኝ።" አለ። "በአላህ ላይ ከእውነት ውጭ አለመናገር ተገቢዬ ነው። ከጌታችሁ የሆነ ተአምራትን ይዤ ወደናንተ መጥቻለሁ። የእስራኤልን ልጆች ከኔ ጋር ላካቸው" አለውም "። (ሱረቱል አእራፍ፡ 104-105)**

ፈርአውን አብሪተኛ ግለሰብ ስለነበር ነብዩላህ ሙሳ ያሉትን ከመቀበል አሻፈረኝ አለ። እሱ ከሁሉም በላይ ሀያል እንደሆነ በማሰብ አላህ ላይ አመፀ። አላህ ነው ለፈርአውን ስልጣን፣ ሀብትና መሬት የሰጠው። ነገር ግን ፈርአውን ይህንን ለማወቅ የሚስችል ንቃተ ህሊና አልነበረውም።

ፈርአውን ከዚህም ይባስ ብሎ ሀሩንና ሙሳ የሱን ግዛት ለማፍረስ የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው በማለት እነሱን ለመክሰስ ፈለገ።

ከዚህ ሁሉ በኂላ አላህ የተለያዩ ቅጣቶችን ወደነዚህ ህዝቦች ላከ።

ይህ ሁሉ ቢከሰትም ፈርአውን እና ህዝቦቹ በነዚህ ቅጣቶች ሊታረሙ አልቻሉም። ወደአላህ ከመመለስ ይልቅ በእብሪተኝነታቸው ቀጠሉበት።

ነገር ግን ይህ ለብዙ ጊዜ አልቆየም...

እነዚህ ሁሉ ነገሮች ፈርአውን ላይ ቢከሰቱም ፈርአውን የአላህን ሀይል  አልተቀበለም። በመጨረሻም አላህ ሙሳን የእስራኤል ልጆችን ይዘው ከግብፅ እንዲወጡ አዘዛቸው።

ሙሳም ህዝቦቻቸውን ይዘው ከግብፅ መውጣት ጀመሩ፡፡

ነገር ግን ፊርአውን ይህንን ጉዞ አልተቀበለውም፡፡ምክንያቱም እሱ ፈቃድ ስላልሰጠ ነበር፡፡ እናም ሙሉ ጦሩን በማዘጋጀት የእስራኤል ልጆችን ለማስመለስ ወጣ፡፡

ሙሳና የእስራኤል ልጆች በባህር እና ከጀርባ በሚመጡ የፊርአውን ሰራዊት እጣብቂኝ ውስጥ ገቡ፡፡ ነገር ግን በዚህ ሲታይ የማይቻል በሆነ ሁኔታ እንኳን ነብዩ ሙሳ በአላህ ላይ ያላቸውን እምነት ወይም ተስፋ አላጡም፡፡

አላህ ተዓምር በመፍጠር ባህሩን ለሁለት ቦታ ከፍሎ አማኞች እንዲያልፉ አደረገ፡፡ ይህ አላህ (ሱ.ወ) ለሙሳ ከሰጣቸው ተዐምራት ውስጥ አንዱ ነው፡፡

አማኞች እንዳለፉ ባህሩ ተጋጠመ አማኞችን የሚያሳድዱት ፊርኦውንና ህዝቦቹ ሰመጡ፡፡

ይህ ተአምር በቁርአን እንደሚከተለው ተገልጿል::

"እንደ ፊርዐውን ቤተሰቦች እና ከርሱ በፊት እንደኖሩት የአፅማያን የአመፅ ልምድ የጌታቸውን አናቅፅ አስተባበሉ፡፡ በሀጢያቶቻቸው ሳቢያም አጠፋናቸው፡፡ የፊርአውንን ቤተሰቦች ውሀ ውስጥ አሰጠምን፡፡ ሁሉም በዳዮች ነበሩና፡፡"(ሱረቱል አንፋል፡54)

ፊርአውን ሊሞት እንደሆነ ሲረዳ በአላህ እንዳመነ በመናገር አላህ እንዲያድነው ተማፀነ፡፡ ነገርግን በዚህ የመጨረሻ ደቂቃ ያደረገው ተውበት ምንም ሊጠቅመው አልቻለም፡፡ ምክንያቱም አላህ (ሱ.ወ) ስህተታችንን የሚምረን በሰራነው ስራ ከልባችን ስናዝን ነው፡፡ አላህ መሀሪ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ግለሰብ ሊሞት እንደሆነ ሲያውቅ የሚያደርገው ተውበት ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህ ነው ፊርአውን ላይ የተከሰተው፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ መርሳት ያሌለብን ነገር አለ፡፡ህይወታችንን መኖር ያለብን አላህን በሚያስደስት መልኩ ነው፡፡ ፊርአውን የሰራውን ስህተት መድገም የለብንም ኑሮአችንን በቁርአን ላይ ባሉት ብፁዕ አስተምህርቶች ካልመሰረትን እና ትዕዛዛቱን ካልተከተልን በመጫረሻው የሞታችን ሰዓት ላይ ብንመለስ ምንም አይጠቅመንም፡፡

## ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ)

ከአላህ ዘንድ ወደ ሰው ልጆች ለመጨረሻ ጊዜ የተላኩት ነብይ ነብዩ መሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነበሩ፡፡

የመጨረሻው ቅዱስ መፅሀፍም ቁርአን ነው።

ከቁርአን በፊት የተላኩ መፅሀፎችን መጥፎ አላማ ያላቸው ሰዎች በርዘዋቸዋል። ስለዚህ ለቀደምት ሕዝቦች የወረዱ መፅሀፎች ትክክለኛ እና ዕውነተኛው ራዕይ በአሁኑ ሰዓት አይገኙም። ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) ሊቀየር እንደማይችል የገለፀልንን ቁርአን አወረደልን። ጌታችን ቁርአንን እንደሚጠብቀው ገልጿል፡-

"መልዕክቱን ያወረድነው እኛ ነን።ከመበከልም በእርግጥ እንጠብቀዋለን።"(ሱረቱል ሂጅር፡9)

እኛ የሚለው ቃል አላህን ያመለክታል። ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም። አጋርም ሆነ ረዳት የለውም። አቻ በሌለው የበላይነቱና ገደብ በሌለው እውቀቱ እና ሀይሉ እሱ ብቸኛ አምላክ ነው።

የመጨረሻው ነብይ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከ አንድ ሺህ አራት መቶ አመታት በፊት ኖረዋል።ስለ እሳቸውም ብዙ መረጃዎች አሉን።

ነብያችን በአላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ ዕውነታዎችን በጊዜው ለነበሩ ሰዎች በማስተማር አላህን (ሱ.ወ) እንዲያመልኩ አስተማሩዋቸው። አላህ ለሰጣቸው ማለቂያ የለሽ ፀጋዎች እንዲያመሰገኑት አዘዟቸው።ከሞት በኋላ ባለው ቀጣዩ አለም ደስተኛ መሆን ከፈለጉ አላህን መታዘዝ እንዳለባቸው ነገሯቸው።

ነገርግን የተወሰኑ ዕብሪተኛና ክፉ ሰዎች ጥሪያቸውን አልተቀበሉም። በርካታ ጉዳቶችን

በማድረስ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ካደጉባትና ከተወለዱባት የመካ ከተማ እንዲወጡ አደረጓቸው። ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) እነዚህን  መጥፎ አላማ ያላቸው ሰዎች እስልምናን እንዲያጠፉ ስላላስቻላቸው ሀይማኖቱ ምንም ሳይቀየር እኛ ዘንድ ደርሷል።

ረሱል ከመካ ወደ መዲና ተሰደዱ እዛም ሰሀቦች ረዷቸው።

የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) መልእክት አሁን ላሉት ሰዎች በሙሉ ይሆናል። የአላህን ምህረት የሚፈልጉ አላህን የሚፈሩ ሰዎች ሊከተሏቸው ይገባል።

“በላቸው፡-አላህን የምታፈቅሩ ከሆናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ያፈቅራችኋል፤ ሀጢአቶቻችሁንም ይምራል፤አላህ መሀሪ አዛኝ ነው።”(ሱረቱል ኢምራን፡31)

ስለዚህ ልጆች አላህ እንዲወደን ከፈለግን በቻልነው ያህል ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ያሉንን መፈፀም አለብን፡፡

## መደምደሚያ፡-

ውድ ጓደኞቼ በዚህ ፊልም ላይ የተወሰኑ ነብያቶችን ብቻ ነው ያየነው፡፡
በታሪክ ጊዜያት ሁሉም ነብያቶች ህዝቦቻቸው አላህን እንዲያመልኩ ተጣርተዋል፡፡ይህን ሀላፊነታቸውን በመወጣታቸው ከህዝቦቻቸው ምንም አይነት ጥቅምን አልፈለጉም፡፡

እነዚህ ነብያቶች የአላህን መልዕክት በማድረሳቸው የሚያገኙት አለማዊ ጥቅም አልነበረም፡፡ሀላፊነታቸውን የተወጡት አላህ (ሱ.ወ) ለዚህ አላማ ስለላካቸው ነበር፡፡ አላህን ይወዳሉ አላህም እንዲወዳቸው ይፈልጋሉ፡፡

ነብያቶቹ የተናገሩት እኛንም ይመለከታል፡፡ ቁርአንን በማንበብ ከነቢያቶች ህይወት ምሳሌ መውሰድ ይኖርብናል፡፡ በዚህ መንገድ በቀጣዩ አለም ደስተኛ መሆን እንችላለን፡፡

አሁን ገና ልጅ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን ሰዎች እናንተንም እማማ ወይም አባባ እያሉ እንደሚጠሯችሁ አትዘንጉ፡፡

እናንተ ስለሞት ለማሰብ ገና ናችሁ ብለው የሚናገሩ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ነገር ግን አላህ አንድ ሰውን መቼ እንደሚወስደው እንደማያውቅ እንዳትረሱ፡፡በአንድ ቀን ወይም በአስር አመታት ውስጥ ልትሞቱ ትችላላችሁ፡፡እነዚህ ነገሮችን ስታስቡ አላህ የሚፈልገው አይነት ሰው ለመሆን ምንም ጊዜ ማጥፋት እንደሌለባችሁ ትረዳላችሁ፡፡

ስለዚህ ጊዜ ማጥፋት የለባችሁም፡፡እነዚህ እውነታዎችን በማሰብ አላህ የሚፈልገው አይነት ሰው ሁኑ፡፡